የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

ስማችን - ኢ.ወክንድ
ልሳናችን - ነቅንቅ

# የአኝዋክ ወገኖቻችን ንፁህ ደም

# ዛሬም ትኩስ ነው !

## ልዩ መግለጫ

ታህሣሥ 2003

EPRPYL

በምዕራቡ የኢትዮጵያ ግዛት ለሀገራቸው ቀናዒ የሆኑት የአኝዋክ ተወላጆች ÷ በዘመናዊዎቹ የትግራይ መሳፍንት የዘር ማጥፋት ፍጅት ከተካሄደባቸው እነሆ ሰባት ዓመት ሞላው::

ጊዜ ዘልዛላ ነው የሚባለውን አባባል ዕውነትነቱን ያረጋግጣል :: የወንድሞችና የእህቶቻችን ደም ሳናስከብር ሰባት ዓመት እንደ ዘበት ሊሞላው ነው ::

የወንድሞቻችንን ደም አፍስሰው የጠጡ ወያኔዎች ዛሬም ያለፍርድ ተንሰራፍተው ስናያቸው÷ በሀፍረት እንሸማቀቃለን:: እነሆ ንጥር ኢትዮጵያውያን የጋምቤላ ልጆችን ዘር አጥፍቶ÷ ለም የሆነውን ምድር ለባዕድ የሸጠ ወያኔ ከነግም ሥርዓቱ እስከ ዛሬ መቆየቱን ስናይ ክፉኛ ይፈታተነናል :: ከሰባት ዓመት በፊት ያን ገራገር ምድር ሸጦ ከማሌሽያ ኩባንያ ቀብድ የበላው እናት- ሻጭ ወያኔ በቅድሚያ ምድሩ ላይ ያሉትን ባለቤቶች መጥረግ ነበረበትና አኝዋኮቻን ፈጃቸው :: ሴት÷ እናት እህቶችን በባለቤቶቻቸውና በወንድሞቻቸው ፊት በዚሁ የወያኔ ጉጅሌ ታጣቂዎች ተደፈሩ :: ተቀጠቀጡ :: ምንም መከላካያ የሌላቸውን ንፁህ ዜጎችን ዘራቸውን አጠፉ::

በእነ መለስ ዜናዊ መሐንዲስነት በነ ዶክተር ገብረአብ ባርናባስ ፈታውራሪነት የተካሄደውን የዘር ማጥፋት ወንጀል÷ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት <u>እንደዋዛ አይመለከተውም</u> :: ዛሬ÷ የሰባተኛ ሙት ዓመትን ስናስታውስ÷ የሚወዷቸውን ልጆቻቸውን÷ የሚያፈቅሯቸውን ወላጆቻቸውን ÷ እንዲሁም ከውስጣቸው ጥልቅ ሀዘን የተሰማቸውን ወገኖች በሙሉ መፅናናቱን ይስጣቸው ስንል ÷ ከዚህ ጋር ተዳምሮ ሌሎቹ ከፍተኛ የሆኑ በደሎችና ወንጀሎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በማካሄድ ላይ የሚገኘውን ይህንን ዘር-አጥፊ ዘረኛ ፋሽስት ሥርዓት ከነግሳንግሱ ለመጥረግ ቁርጠኛነታችንን በመግለጽ ነው ::

አማራን ከነነፍሱ ጉድጓድ መክተት÷ ኦሮሞን በጅምላ መጨረስ÷ ኦጋዴንን መጨፍጨፍ÷ የአኝዋክን ዘር ማጥፋት÷ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ጨርሶ ለማጥፋት ከአቀደው የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ጋር የተየያዘ ነው :: ይህ ርምጃ የብሄር- ብሄረሰብ እኩልነት ሳይሆን ÷ ተራ የወያኔ የአባባል ቅርሻት ከመሆን አይዘልም ::

የዛሬ ሰባት ዓመት ከተፈጁት አራት መቶ አኝዋኮች ዛሬ በሕይዎት ቢኖሩ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወጣቶች ነበሩና ÷ ዛሬ ለሚደረገው የነፃነት ትግላችን ይቀላቀሉን እንደ ነበር ጥርጥር የለንም :: ይህንንም የመሥዋዕት ዝክር ስናስታውስ ÷ እንደ ዜጋ ብቻ ሳይሆን ÷ እንደ አቻ ጓደኞቻችንን ቁመን እንዘክራቸዋለን ፤ ይህንን መግለጫ የምናወጣውም ÷ ለአትርሱን ሳይሆን ÷ ለአንረሳቸውም ጥሪ ማስተጋቢያ ይሆናል ::

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@google.com
www.eprpy.com

ውድ ኢትዮጵያውን ጋምቤላዎች ሆይ !

የኢሕአፓ የምጥ ግልገሎች የሆን ወጣቶች ነንና፥ አፍላም ነንና፥ ለአኝዋክ ሕዝብ በደል፥ ለአኝዋክ ከመሬታቸው መፈናቀልና ድንግል መሬት መቀማት በተገኘው ጊዜና ቦታ በደማችን ልንታደግ ቃል እንገባለን ። በዚህ አጋጣሚ ፥ለአኝዋክ ወጣቶች ዜጎቻችን በየትኛውም አመች ጊዜና ቦታ ከኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት ጋር ለመቀላቀል ስትሹ፥ በራችንን ከፍተን፥ እጃችንን ዘርግተን እንቀበላችኋለን ። እናብራለንም ፥ እንደራጃለንም፥ እንታገላለንም፥ እናቸንፋለንም ። ይህ ነው ጥሪያችን !

የወያኔ ሃርነት ትግራይን እንደ መንግሥት ቆጥራችሁ የጋምቤላን መሬት የገዛችሁ፥ ህንድ ተባላችሁ ቻይና ፥ ዐረብ ተባላችሁ ሌላ ፥ ለቃችሁ ትወጡ ዘንድ የትህትና ጥያቄያችንንስናቀርብ ፥ ኋላ ለሚደርሰው ጥፋትና ጥቃት ፥ የጋምቤላ ሕዝብን እንዳትጠይቁ አደራ እንላለን ።

የወያኔ መውደቅና የውላቸሁ መቀደድ በአንድ ላይ እንደሚከሰት ከወዲሁ ማሳሰቢያ እንሰጣለን ።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት እኩልነት

ደማችንን አንሳሳለትም !

የአኝዋኮች ነፍስ ፍርድ ታገኛለች !

ደማቸውንና ደማቸው ደማችን ነውና እንበቀላለን !

ኢ- ወክንድ

EPRPYL

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@google.com
www.eprpy.com